**እሳት አመድ ወለደ**

**ለተማሩ ለማይማሩ አፈ ሊቃውንት ( ፲፱፻፹፡ አዲሳባ ) ከእሣት ወይ አበባ**
**በሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን**

አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል !
ወለድኩ ይበል ይልቅ፤ በቃ፤
በምላሱ የሚያመርቃ !
ወኔው በአረቄ እሚነቃ
ልቡን በቧልት እሚደቃ
በሜራ በነገራ አሽሙር
' በታክት በእንትሪንግ ' አዙር
ሳሮጥ ሳሽከረክር ሳዞር
በብልጠት በአንደበት ንቃት፤ በመስሎ አስመስሎ መኖር
ሴቷን በነገር መብለጥለጥ ጋለሞታን በምላስ ጦር
ሁሏን ረትቼ አሸንፌ፤ በምጸት ወግ፤ በጌጥ፤ በ ' አሞር '
ሲነጋ እንደ አመድ አፋሽ ገል
ሲመሽ እንደ ሽንቁር በርሜል
የአግቦ ጢስ በማንቃረሩ
ወሬ በማንሸራሸሩ
ተሞልቶ በመተርተሩ፤
ነፋስ ጠብቶ አየር ታልቦ
የነገር ረሃብ ተርቦ
ጉድ በማናፈስ ተስቦ
ከዚህ ቀዶ እዝያ ዘንቦ _ _ _ _
ውሃ እንደ ማይቋጥር ገንቦ
ላባቴ ተወልጄለት ቅምትል የልቡ ኩራት
ግስላው የወኔው እሳት
ይመካ እንጂ ይንቀባረር
ይሞካሽ እንጂ ይገደር
የዘር ወጉ እንዳይደፈር
ደርሼለት እሱን መሰል
በተከለው የሚከተል
አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል ።
መድሰል ወራሽ ወለድኩ ይበል፤ የዘር ቅርሱን የሚያስፋፋ
ድል የሚመታ ሰተቴ፤ በነገር በአሽሙር ልፈፋ
በአግቦ እንደ ቅኔ ዘረፋ
በሽሙጥ ባፍ ዘለፋ፤
ይበል እንጂ ' እኔም ወንድ ወለድኩ
ባፍ እሚበልጠኝ አደረስኩ
ያባት ልጅ ያዘው ቅምጥል '
የደሙ ትክል የወኔው ሽል፤
ፈጠርኩ ይበል ቀበዝባዛ እንደአዙርት እሚፈትል

በምላስ ቀስት አነጣጥሮ፤ ቂም በልቦና እሚተክል
ደም በደም እሚያስተጣጥብ፤ ወገን ከወገን እሚያክል
እንደ ሠራ ሠር ደብተራ፤ ላንቃው መርዝ እሚያቀላቅል
ውጋቱ ዘር እሚያጣጥል
እንደጦስ እሚደበልል
እንደዛር ውላጅ አሽሮ
ያጥንት ስባሪ አቅሮ
ደም መራዥ ልጅ ያፋፍ ላይ ድጥ
መስክ መሳይ ያሽሙር ደለል፤
የወሬ ማንፊሻ ጋሻ ፤ ደርሼለት እሱን መሰል
በተከለው እሚተክል _ _ _
አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል " !